የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ካሉ አስራ ሁለት ክልሎችና ሁለት የከተማ አስተዳደር አካባቢዎች በስተሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኝ ክልል ነው፡፡ ክልሉ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ የራሱን ክልል በማደራጀት በህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠውን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህ መሰረት የክልሉ ህዝብ የጤና አግልግሎት ተጠቃሚነትን ለማረጋጋጥ ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ እና ቀበሌ የጤና ስርአት በመዘርጋት እና የሰው ሃይል በሟሟለት ዘርፉ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡
በመሆኑም በክልላችን 2 ሆስፒታሎች፣ 3 ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም 32 ክሊኒኮች ብቻ የነበሩ ሲሆን መንግስት ለጤናው ዘርፍ በሰጠው ትኩረት መሰረት ይህ ቁጥር በአሁኑ ሰዓት 2 አጠቃላይ ሆስፒታሎች እና 4 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ፤ 60 ጤና ጣቢያዎች እና 426 ጤና ኬላዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉና ሌሎች በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ የጤና አገልግሎት አሰጣጠንም ለማሳለጥ በየተቋማቱ የሰለጠነ የጤና ባለሙያዎች ተመድበዉ ለማህበረሰቡ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በክልሉ በሚገኙ ቀበሌዎች 1028 የጤና ኤክስቴንሽን ሙያተኞች ተመድበው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን እየሰሩ በመፈፀም ላይ ይገኛሉ፡፡

ክልሉ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከማሳካት አንጻር ደግሞ በጤና ዘርፍ የእናቶች እና የህጻናት ጤናን ማሻሻል እና ሞትን መቀነስ፣ ኤች አይቪ ኤድስ መከላከል፣ የወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር፣ የፖሊዮ በሽታን ማጥፋት፣ የእናቶች እና የጨቅላ ህጻናት መንጋጋ ቆልፍ ማጥፋት፣ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ ተደራሽ ማድረግ እና የፆታን እኩልነትን ለማረጋጋጥ የተቀመጡ ግቦች ማሳካት ተችሏል፡፡

በተባበሩት መንግስታት የተቀመጠውን ዘላቂ ልማት ግቦች (SDG) ለአብነት ያህል የእናቶች እና የህጻናት ጤናን ማሻሻል እና ሞትን በመቀነስ፣ ተላላፊ በሽታዎችን በመቀነስ፣ የስነ ተዋልዶ ጤናን እና መሰረታዊ የጤና አግልግሎት ተደራሽ በማድረግ በኩል አበረታች ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አወቃቀር በሰሜንና ሰሜን ምስራቅ አማራ፣ በምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ኦሮሚያ እና በደቡብ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልሎች የሚያዋስኑት ሲሆን በምዕራብ ከሱዳን ሪፐብሊክና በደቡብ ምዕራብ ደግሞ ከደቡብ ሱዳን ጋር ይዋሰናል፡፡ የክልሉ የቆዳ ስፋት **50381** ስኩዌር ኪ/ሜ ሲሆን የአባይ ወንዝ ክልሉን ለሁለት ከፍሎ ወደ ሱዳን ይፈሳል፡፡ ፻ዚህም አኪያ

በክልሉ ሰሜናዊ ክፍል የመተከል ዞን 26560 ስ.ኪ.ሜ የቆዳ ስፋት ሲኖረው በደቡባዊ ክፍል አሶሳ ዞን፣ ካማሽ ዞንና ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ 23820 ስ.ኪ.ሜ ስፋት አላቸው፡፡ በመልከዓ-ምትራዊ አቀማመጡም በ□ም ዌቅተኛ በሆኑ ቦታች እስከ 580 ሜትር በከፍተኛ ቦታች ደግሞ እስከ 2731 ሜትር የሚደርስ ሲሆን የክልሉ ከፍተኛ ቦታ በዳንጉር ወረዳ የበለያ ኙላቶ ሲሆን ዝቅተኛ ቦታዎች የአባይ ወንዝ ከኢትዮጵያ በሚወጣባቸው አከባቢ የሚገኙ ናቸው፡፡

ዋና ዋና የአየር ንብረቱም 75 በመቶ ቆላ/ ከ1500 ሜትር በታች/፣ 24 በመቶ ወይና ደጋ/ ከ1500 -2300 ሜትር/ እና 1 በመቶ ደጋ/ ከ2300 ሜትር በላይ / ሲሆን አማካይ የሙቀትና የዝናብ መጠን በቅደም ተከተል ከ17□ ሰ - 29 □ ሰ እና ከ860 - 1600 ሚ.ሜ የሚደርስ ሆኖ የዝናብ ስርጭቱ ከስድስት እስከ ሰባት ወራት ያህል ይቆያል፡፡

□ልሉ □ተለ□□ ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ ቅርሶች ባለቤት ሲሆን በተለይ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደነቀውና በርዝመቱ ተወዳዳሪ በማይገኝለት የአባይ ወንዝ ላይ □እየተሰራ □ለው ታላቁ የኢትዮጵያ ህ□ሴ □ትብ መ□ኛ በመሆኑ ግድቡ ሲጠናቀቅ ከፍተኛ የቱሪስት መስህብ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የከበሩ ማዕድናትን ና ሰፋፊ የእርሻ ልማት ባለቤት ነ□ ፡፡

የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት በሶስት እርከን የተዋቀረ ሲሆን እነዚህም የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ናቸው፡፡ በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ 368 ጤና ኬላዎች፣ 47 ጤና ጣቢያዎች እና 6 ሆስፒታሎች ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ሲሆን አጠቃላይ የጤናው ዘርፍ ሰራተኞች ቁጥር 7,456 ገደማ ነው፡፡

የጤናው ዘርፍ ራዕይ ጤናማ፣ አምራች እና የበለፀገ ህብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት ሲሆን ተልዕኮውም ጥራቱን የጠበቀ፤ ፍትሐዊና ተደራሽ የሆነ የተሟላ የጤና አገልግሎት በመስጠት ፤ በሽታዎችን በመከላከል እና በመቆጣጠር የህዝቡን ጤናና ደህንነት መጠበቅ ነው፡፡ የጤናውን ዘርፍ ተልዕኮ ለማሳካት የሚከተሉት እሴቶች ተለይተዋል እነሱም፡- ቅድሚያ ለማህበረሰብ መስጠት፣ ተባባሪነት፣ ሩህሩህነት፣ ሙያ አክባሪነት፣ ሚስጥር ጠባቂነት፣ ህግ አክባሪነት እና አለማዳላት ናቸው፡፡ እንዲሁም የጤና ስርዓቱ መርሆዎች ጥራት፣ ፍትሃዊነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልፀኝነት፣ ቀጣይነት፤ የጤና ትምህርት ላይ የተመሰረተ እና ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ ናቸው፡፡

በሀገራችን ብሎም በክልላችን እ.ኤ.አ ከ1997 ጀምሮ በየአምስት ዓመቱ በአራት ዙሮች ተከታታይ የሆነ የጤናው ዘርፍ የልማት ፕሮግራሞች (ጤ.ዘ.ል.ፕ1--ጤ.ዘ.ል.ፕ4) ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ጤ.ዘ.ል.ፕ4 እ.ኤ.አ 2015 የተጠናቀቀ ሲሆን የክልሉ የዕድገትና

ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አካል ነው፡፡ የአራቱም የጤናው ዘርፍ የልማት ፕሮግራም ትግበራ ከተጠናቀቀ በኋላ እ.ኤ.አ ከ2015/16-2019/20 የመጀመሪያው የጤናውን ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም እ.ኤ.አ ከ2020/21-2024/25 ሁለተኛው የጤናው ዘርፍ ትራንፎርሜሽን ዕቅድ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ አሁን ካለንበት ሁኔታ በመነሳት ሁለተኛውን የጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ጤዘትዕ-II) እንደገና ማየት እና ከ2016 እስከ 2018 በጀት ዓመት የሚቆይ ለሶስት ዓመት ተግባራዊ የሚደረግ የጤና ዘርፍ መካከለኛ ዘመን ልማት እና ኢንቨስትመንት ዕቅድ (ጤመዘልኢእ) ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

ይህንን ዕቅድ ለማዘጋጀት በዋናነት ከሚጠቀሱት ምክንያቶች መካከል ከመንግስት ክልላዊ እና አገራዊ የልማትና ኢንቨስትመንት ዕቅድ ጋር ማጣጣም አስፈላጊ በመሆኑ፤ ባለፉት ሶስት ዓመታት የጤና ስርዓቱ ፈታኝ በሆኑ ወረርሽኞች (ኮቪድ-19 እና ሌሎች ወረርሽኞች) መከሰት ክፉኛ የተጎዳ በመሆኑ፤ በተለያዩ የክልላችን ዞኖችና ወረዳዎች በተከሰቱ ግጭቶች ሳቢያ መፈናቀል፤ የጤናው መሰረተ ልማት ላይ የደረሱ ጉዳቶች ተጽዕኖ መፍጠር እና ይህንንም ለመቋቋምና የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ የጤና ዘርፍ መካከለኛ ዘመን ልማት እና ኢንቨስትመንት ዕቅድ (ጤመዘልኢእ) ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

ይህ የጤናው ዘርፍ መካከለኛ ዘመን የልማት እና ኢንቨስትመንት ዕቅድ (ጤዘልኢዕ) በሚቀጥሉት ሶሰት ዓመታት ማለትም ከ2016-2018 በጀት ዓመት የሚቆይ ክልላዊና ሀገራዊ የጤናው ዘርፍ ስትራቴጂክ ዕቅድ ነው፡፡ ዕቅዱም የተዘጋጀው የጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን ዕቅድን (ጤዘትዕ-II) ያለፉት ሶስት ዓመታት አፈፃፀም እና የሁኔታ ትንተና እና ግምገማ እንደ መነሻ በመውሰድ ነው፡፡

የጤና ዘርፍ መካከለኛ ዘመን ልማት እና ኢንቨስትመንት ዕቅድ ዝግጅት የአሥር ዓመት የጤናው ዘርፍ ልማት ዕቅድ፣ ሀገር አቀፍ ሁኔታዎችን መነሻ በማድረግ እና የዘላቂ የልማት ግብ (SDGs) ከግምት ውስጥ በማስገባት ታቅዷል፡፡ በዕቅድ ዝግጅቱ ሂደት ላይ የክልሉ የጤና ቢሮ የስራ ክፍሎች እና የልማት አጋር ድርጅች ተሳትፈዉበታል፡፡የጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ጤዘትዕ-II) ሁኔታዊ ትንተና ላይ በመመስረት የልማት እና ኢንቨስትመንት ዕቅዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ ዓላማዎች፤ ኢኒሼቲቭ፤ ዋናዋና ተግባራቶችን ለማመላከት ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም በክልላችን በቅርብ ጊዜ የተካሄዱ የዳሰሳ ጥናቶች እና በየጊዜው በመደበኛው የጤና መረጃ ስርአት የሚመጡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከአላማዎች አቀማመጥ ጋር በተያያዘ የባለፉትን ሶስት ዓመታት የአፈጻጸም

አዝማሚያዎች፣ የሚገኝ ሀብት፤ ክልላዊ እና አገራዊ ስምምነቶችን፣ የአስር አመት የጤናው ዘርፍ ልማት ዕቅድ የክልሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቷል። የልማት ዕቅዱ የኢንቨስትመንት የወጪ ተመን የተዘጋጀው የፕላንና እና ልማት ቢሮ  ቅጻ ቅፅ በመጠቀም ሲሆን በተጨማሪም የጤናው ዘርፍ የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ጤዘትዕ-II) ሰነድ ዝግጅት ወቅት ጥቅም ላይ የዋለውን ዋንሄልዝ ቱል (OneHealth tool) በመጠቀም ማዘጋጀት ተችሏል።

ይህ ሰነድ በሰባት ምዕራፎች የተደራጀ ሲሆን ምዕራፍ አንድ መግቢያ፤ ምዕራፍ ሁለት የሁኔታ ትንተና እና የባለፉት ዓመታትን አፈፃፀም፤ ምዕራፍ ሶስት ግቦችን፣ ኢላማዎችን፣ ፕሮግራሞችና ስትራቴጂክ ኢኒሼቲቭ እና ዋና ዋና ተግባራት፣ ምዕራፍ አራት የአፈፃፀም መለኪያዎችን እና ዐዒላማዎች፣ ምዕራፍ አምስት የኢንቨስትመንት እቅድ ከወጪ ዝርዝር እና የፋይናንስ ክፍተትን በማካተት ሲቀርብ፣ ምዕራፍ ስድስት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች እና የስጋት መቀነሻ ስልቶች፣ በምዕራፍ ሰባት የዕቅድ ክትትልና ግምገማን የሚዳስስ ክፍሎችን በማካተት የተዋቀረ ነው።